ይድረስ ለተከበሩ አባቴ ለንቡረዕድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ !

<ያመ ኢትዮጵያ> <ኢትጵያዊዉን ችግር በኢትዮጵያኛ መላ> ብለዉ ያቀረቡልንን ፅሁፍ በጥልቀት አንብቤዋለሁ፡፡ ፅኑፉን እንዳነበዉ በድረገፅ ላይም መለቀቁን ስልክ በመደወል ያበሰረችኝ የእርስዎ ልጅ እህታችን ሀይማኖት ናት፡፡ ፅሁፉን በርካታ ሰዎች እንዲያነቡት በኢሜይል በመላክና በሃርድ ኮፒ በማባዛት እንዲሁም በጉባኤያችን ላይ በመወያዬት በርካታ ኢትዮጵያዊ ቢደርሰዉ ብለን እየሞከርን ነዉ፡፡ ምንም እንኳን የነነዌ ያም ወቅት ያለፈ ቢኖንም የጽሁፉ መልዕክት ጠንካራና ቀጣይነት ያለዉ ስለሆነ አሁንም ለብዙ ሰዎች ቢደርስ ኢትዮጵያዊዉ አምላኩን አሁንም እንዴት በፅናት መለመን እንዳለበጽ ያሣሥባል፣ ይመራል እንዲሁም ያነሳሳልና፡፡

የተከበሩ አባቴ ንቡረዕድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ !

በእዉነቱ እያደረጉ ያለዉ አስተዋፅኦ ምን ያህል መሰረት ያለዉ ፣ ያማይናወፅ ሡብእናን ለመፍጠርም ወሳኝና በሀይል ምንጭ የሚያጥለቀልቅ እንደሆነ ልገልፅለዎት እወዳለሁ፡፡ ይሄም የነገርን መነሻ እና መድረሻ አንዱን እና ብቸኛዉን አምላክ ፥ ንጉሰ ነገስቱንና የካህናት ካህን የሆነዉን ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ተብሎ የሚጠራዉን ኢየሱስ ክርስቶስን ዋልታና ምሰሶ አድርገዉ ይዘዉ በመነሳትዎ ነዉ፡፡ ይሄም ትምህርትዎ እንዲሁም በዘመኑ ሰዎች ቋንቋ ለእኔ በግሌ በሚገርም ሁኔታና ላምነዉ በማልችለዉ መጠን ፍልስፍናዬ ፣ እምነቴና የቀን ከቀን መርሄ ወደመሆን መለወጡ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ወንድሞቼም ለማካፈል በዉስጤ የሚገርም መነሳሳትን መፍጠሩ ለራሴም እንኳን ይደንቀኛል፡፡ የእርስዎን መፅሀፍት ካነበብሁ ብሁላ ( ማለትም ኢትዮጵያ የአለሙ መፋረጃ ፣ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ) ምን ያህል የተደበቁ ሚስጥራት ያሏት ታላቅ ሀገር እንዳለችን መረዳት ብቻ ሳይሆን ይሄን ሚስጥሯን ደግሞ አንዳንዶች ባለማወቅ ፣ ሌሎች በምቀኝነትና በቅናት ፣ ሌሎች ደግሞ በንዝህላልነትና ባለማስተዋል ሊያዳፍኑትና ሊያጠፉት እንደሚዉቾረቾሩ ማስተዋል ችያለሁ፡፡

መቼስ እግዚአብሔር የሚናገር በአንድም ወይም በሌላ መልክ አይደል ? ህዝቡን የሚጠብቀዉ በአንድ ሰዉ ትምህርት ሊሆን ይችላል፡፡ ለሀገሪትነ ኢትዮጵያም ይሄን በማድረጉ ለእሱ ለአምላካችን ምስጋና ይግባዉ፡፡ ቢያንስ አንድ እርስዎን በመፅሀፍትዎ በኩል የሚያያዘንቡልንን ትምህርት በጥቂቱም ቢሆን ለምናደምጥ ኢትዮጵያዊያን አስነስቶልናልና፡፡ በእዉነቱ የፃፉቸዉ መፅሃፍት እንዲሁም አሁን የፃፉት ፅሁፍ ግሩምና ድንቅ ነዉ፡፡ እግዚአብሔር አሁንም አብዝቶ በረከቱን ያፍስስልዎት፡፡

ከዚህ በመቀጠል የሚከተሉትን ሁለት ነጥቦች ላነሳልዎት እወዳለሁ፡

1ኛ) በሀገር ዉስጥ ማለትም በኢትዮጵያ ጋዜጣና መፅሄት ስለማዘጋጀት ነዉ፡፡ በአሁኑ ሰአት አብዛኛዉ ኢትዮጵያዊ የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን ማግኘት ይፈልጋል፡፡ በተለይም እንደርስዎ ፅሁፍ በሀይል ፣ በዕምነትና መሰረታዊ የፍልስፍና መልህቁን በማይናወጥ መልኩ ማስረዳት የሚችል ፅሁፍ ህዝቡ በጣም ያስፈልገዋል፡፡ ይህም ለቅዱሱ ህዝብ ኩራትና በራስ መተማመንን የሚፈጥር ሲሆን የቅዱሱ ህዝብን ማንነት ለማዉደም ለሚራወጡ ወገኖች ደግም አንገት አስደፊ ነዉ፡፡ ስለዚህ በሀገር ማለትም በኢትዮጵያ ጋዜጣና መፅሄት ማዘጋጀት ቢኖርና ስርጭት ቢደረግ በርካታዉን ህዝብ ማድረስ ይቻላልና ቢያስቡበት፡፡ ብዙዉ ህዝብ ድረገፅ የማያገኝና ኢሜይል የሌለዉ ነዉና፡፡

2ኛ) የቃል ኪዳን ሀገር በሆነቸዉ ሀገራችን ኢትዮጵያ ወደፊት ምናልባት አምላክ ቢፈቅድና ንጉሰ ነገስቱ ኢየስስ ክርስቶስ ኢትዮጵያ በቤተህዝቡ ፣ በቤተ ክህነት እና በቤተ ምልክና የምትመራ ሀገር ቢኖረን እንዴት የተለያዬ እምነት ካለዉ ኢትዮጵያዊ( በርካታ ቁጥር ያለዉ ህዝብ የተዋህዶ እምነት ተከታይ አይደለም- አንዳንድ መረጃዎች እንደሚያሳዩት እስከ 45% የሚሆነዉ ህዝቧ በተዋህዶ እምነት ጥላ ስር አይድለም ) ጋር በእንደዚህ አይነት የእግዚአብሔር ስርአተ መንግስት ስር አብሮ መኖር እንችላለን ? ምክንያቱም አመፅ ማስነሳታቸዉ ፧ በተዋህዶ ስርአተ መንግስት ስር አስገብተዉ

ማንነታችንን ገሰሱብን ማለታቸዉ ፣ በዙሪያችን ካሉ ጠላቶቻችን ጋር በመተባበር ቅድስቲቱን ሀገር ማጥቃታቸዉ መቼም እንደማይቀር ከእርስዎ የተሰወረ አይደለም፡፡ ደግሞም የራሳችን የተዋህዶ ክርስትና ተከታይ ልቡ በፍርሃት መራዱ አይቀርም ፣ እምነቱም በተለያዩ ስንኩል ፍልስፍናዎች መዋለሉ አይቀርም ብሎም እሬትና አሁን እያደረገ እንዳለዉ የተባረከዉን ስርአተ መንግስት(በቤተህዝቡ ፣ በቤተ ክህነት እና በቤተ ምልክና መመራትን ) ለማፍረስ መራወጡ አይቀርም፡፡ እና 45% የሚሆነዉ ህዝቧ በተዋህዶ እምነት ጥላ ስር ባልሆነበት ሁኔታ የተባረከዉን ስርአተ መንግስት በኢትዮጰያ ምድር መመስረት ይቻላል? ወይስ ቅዱሱን ህዝብ በመነጠል በኢትዮጵያን የአተቀደሰዉን ስርአተ መንግስት ማቋቋም ይሻላል? ወይስ 45% የሚሆነዉ ህዝቧ በተዋህዶ እምነት ጥላ ስር ማሰባሰብ የሚያስችል አቅምና ጉልበ ይኖራል? የእነዚህንና ተዛማጅ ጥያቄዎችን መልስ ከእርስዎ ብሰማዉ ደስ ይለኛል፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች በክርስቶስ ፊት ኢምንት እንደኔ በደካማ ሰዉ ዘንድ ግን ከባድ መሆናቸዉ የታመነ ነዉ፡፡ ይህም ሆኖ በሰዉኛ አስተሳሰብ መልስ የሚፈልጉ ነጥቦች ናቸዉና ከላይ ላነሳሁቸዉ ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡኝ በትህትና እጠይቅዎታለሁ፡፡